መልእክት አሥራ ሁለት

**የመልካሚቱን ምድር ድሰታ በተመለከተ**
**በ1ኛ እና 2ኛ ሳሙኤል በሚታዩ አምስት ዋና ስዕሎች**
**ያሉ መንፈሳዊ መርሆች፣ የሕይወት ትምህርቶች እና ቅዱስ ማስጠንቀቂያዎች**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፡- 1 ሳሙ. 2፡27-30፣ 35፤ 3፡21፤ 12፡3-5፣ 23፤
18፡1-4፤ 23፡16-18፤ 9፡1-2፤17፤ 13፡13-14፤ 15፡19፣ 23፤ 16፡1፣ 12-13፤
30፡6-10፤ 26፡19፤ 2 ሳሙ. 11፡1-27

**I. በዔሊ ሥር የነበረው አሮጌው አሮናዊ ክህነት የሻገተ እና የደበዘዘ ነበር (1 ሳሙ. 2፡12-30)፣ እና እግዚአብሔርም ለኢኮኖሚው መፈጸም አዲስ ጅማሬ ለማግኘት ፈልጎ ነበር፡-**

ሀ. ሁላችንም የትኛውንም አይነት መሻገትን፣ እርጅናን፣ ለብ ማለትን፣ እና ትዕቢትን አለመቀበል፣ እና ከጌታ ጋር ባለን ግንኙነት ራሳችንን ባዶ፣ ክፍት፣ ትኩስ፣ አዲስ፣ ሕያው፣ እና እንደ ሕጻናት አድርገን መጠበቅ አለብን፤ ለሕይወታዊው የክርስቶስ አካል ግንባታ ክርስቶስን እንኖር ዘንድ ከክርስቶስ ጋር አንድ ለመሆን፣ በክርስቶስ ለመሞላት፣ እና በክርስቶስ ለመያዝ ከመሻቱ ጋር አንድ መሆን ያስፈልገናል—ራእ. 3፡15-22፤ ሉቃ. 18፡17፤ ፊልጵ. 3፡7-14፤ ገላ. 1፡15-16፤ 2፡20፤ 4፡19፤ ኤፌ. 4፡16።

ለ. በዔሊ ዘመን የእግዚአብሔር ቃል ብርቅ ነበር፤ የእግዚአብሔር ንግግር ከሞላ ጎደል ጠፍቶ ነበር (1 ሳሙ. 3፡1)፤ በክህነት ውስጥ አንድ ካህን ሊያደርገው የሚገባው የመጀመሪያው ነገር ለእግዚአብሔር መናገር ነው (ዘጸ. 28፡30)፤ ካህን ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ ግንኙነት ያለው፣ ከእግዚአብሔር ጋር አንድ የሆነ፣ የእግዚአብሔርን ልብ የሚያውቅ፣ እና ልዩና ብቸኛ የሆነውን ጤነኛ የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ ኢኮኖሚ ትምሕርት የሚናገር መሆን አለበት (1 ጢሞ. 1፡3-4፤ 6፡3)።

ሐ. ዔሊ ሳሙኤልን "አቤቱ፥ ባሪያህ ይሰማልና ተናገር በለው" ብሎ ጌታን እንዲያናግረው አስተማረው፤ ለጌታ ለመናገር እና ዘለለማዊውን ኢኮኖሚውን ለማከናወን ከእርሱ ጋር አንድ ለመሆን መሻቱን እና ምርጫውን እናውቅ ዘንድ በመጀመሪያ ንግግሩን እንደ ውድ መዝገብ መያዝና በትኩረት ማዳመጥ አለብን—1 ሳሙ. 3፡9-10፤ ኢሳ. 50፡4-5።

መ. ዔሊ ክፉ የነበሩትን ሁለቱን ልጆቹን እንደሚገባ ባለመቅጣት ክህነትን ቸል አለ (1 ሳሙ. 2፡28-29)፤ ይህ የእርሱን ታሪክ አሳዛኝ ድምዳሜን፣ የእርሱን የመልካሚቱን ምድር ድሰታ መቋረጥን፣ እና በመለኮታዊው መገለጥ፣ ማለትም፣ ለእግዚአብሔር መናገርን በተመለከተ የክህነት መደብዘዝን አመጣ፤ ዛሬ እግዚአብሔር በምለሳው ለሰጠን ከፍ ያለ ዋጋ እንሰጥ ዘንድ ከዔሊ መማር ያስፈልገናል።

**II. ሳሙኤል በእግዚአብሔር ለተሰጡት ስፍራዎች እና አፊሶች በእግዚአብሔር ፊት ታማኝ ነበር፡-**

ሀ. እንደ አንድ ሌዋዊ በሕይወት ዘመኑ ሁሉ እግዚአብሔርን አገለገለ፤ እንደ አንድ ናዝራዊ መሰጠቱን ያለ ውድቀት ጠበቀ (ቁ. 35)፤ እንደ ካህን-ነቢይ በግልጽነት ለእግዚአብሔር ተናገረ፣ መለኮታዊ መገለጡ እየጠፋ የሄደውን ክህነት ለመተካት ነብይነትን አነሳሳ፤ ለእግዚአብሔር ኢኮኖሚ መሟላት ዘመኑን ለመቀየር መስፍንነትን በመሻር እና ንግሥናን በማምጣት እንደ አንድ መስፍን ለእግዚአብሔር ታማኝ ነበር፣ ለሕዝቡም ፍትሃዊ ነበር።

ለ. ለኢኮኖሚው መከናወን ከእግዚአብሔር ጋር አብሮ እንደሚሠራ ሰው (ዮሐ. 5፡17፤ 2 ቆሮ. 6፡1)፣ የያሕዌን ቃል በመስማት ለእርሱ እንዲናገር ሳሙኤል የያሕዌ ነብይ ተደርጎ ነበር (1 ሳሙ. 3፡9-10፣ 20-21)፤ "መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚናገረውን" ለመስማት (ራእ. 2፡7) ራሳችንን ያለማቋረጥ ማንቃት አለብን፤ በተጨማሪም "ቃሉን ልትሰማ በኢየሱስ እግር አጠገብ ተቀምጣ" (ሉቃ. 10፡38-42) የነበረችውን የማርያምን ምሳሌ መከተል ያስፈልገናል፡-

1. ማርያም _በጌታ ኢየሱስ_ እግር አጠገብ ተቀመጠች እንጂ በሌላ በማንም እግር አጠገብ አልተቀመጠችም፤ ወደ ጌታ አፍታ በአፍታ ከመምጣት፣ እርሱን ከመውደድ፣ እርሱን ከማምለክ፣ እና ከእርሱ ጋር ባለማቋረጥ ኅብረት ከማድረግ እና በመገኘቱ ውስጥ ከመቆየት የሚሻል ሌላ ዘዴ የለም።
2. ማርያም _በጌታ እግር አጠገብ_ ተቀመጠች፤ የጌታን ንግግር ለመስማት እና የእርሱን በረከት ለመቀበል ራሷን ዝቅ ባለ ስፍራ ላይ አስቀመጠች፤ ትሕትና ራሳችንን ማሳነስ አይደለም፤ ትሕትና ራሳችንን ቸል ማለት፣ ራሳችንን መቃረን እና ራሳችንን ምንም እንደሆንን መቁጠር ነው።
3. _ተቀምጣ_ ነበር፡- ከጌታ መገናኘት እስከመራቅ ድረስ የሚስተጓጎሉ ሰዎች ተንከራታች አእምሮ እና የሚዋዥቁ ሃሳቦች አሏቸው፤ በየዕለቱ ከጌታ ጋር የግል ጊዜ ለማሳለፍ ራሳቸውን ማቆም አለባቸው።

4. *የጌታን ቃል ትሰማ* ነበር፡- ጌታ ለእኛ የሚናገራቸው ቃላት መንፈስ እና ሕይወት ናቸው (ዮሐ. 6፡63)፤ ጌታን ራሱን ታገኝ ዘንድ የጌታን ቃል መስማቷ ጌታ ከእርሷ ጋር እንዲነጋገር እና ራሱን ወደ ውስጧ እንዲያድል መልካም አጋጣሚ ሰጠው።

ሐ. ሳሙኤል ከመልካሚቱ ምድር የነበረውን ድርሻውን ለሕይወት ዘመኑ ሁሉ በሙላት ተደሰተ፤ ስለዚህ በአዲስ ኪዳን ቃና የክርስቶስ ድሰታውን በተመለከተ ምንም አይነት እንከን አልነበረበትም ማለት እንችላለን፤ በሳሙኤል ታሪክ ውስጥ የነበረው ብቸኛ እንከን በእስራኤል ልጆች መካከል ሁለቱን ልጆቹን እንደ መሳፍንት መሾሙ ነው—1 ሳሙ. 8፡1-13፡-

1. የሳሙኤል ልጆች ኢ-ፍትሃዊ መንገዶች በሕይወት ዘመኑ ሁሉ አባታቸው ይከተል ከነበረው ንጹህ እና ፍትሃዊ መንገድ (12፡3-5፣23) ተቃራኒ ነበሩ፣ እና የእስራኤል ልጆች እንደ አሕዛብ ሁሉ በእነርሱ ላይ እንዲፈርድ ንጉስ ይሰጣቸው ዘንድ ሳሙኤልን ለመጠየቅ ምክንያት ሰጣቸው (8፡1-7)፤ ስለዚህ የሳሙኤል ልጆች በእስራኤል ልጆች መካከል እንደ መሳፍንት መቆጠር የለባቸውም (ሐዋ. 13፡20)፣ አባታቸው ሳሙኤል እንደ መጨረሻው መስፍን መቆጠር አለበት።
2. እንደ ሰው፣ ሳሙኤል በዚህ ጉዳይ ስህተት ሠራ፣ ነገር ግን ይህ ስህተት ለኢኮኖሚው መሟላት ንግሥናን በማምጣት በሕዝቡ መካከል ያለውን ሁኔታ ለማስተዳደር እግዚአብሔርን ረዳው።

## III. ዮናታን ዳዊትን ወደደው፣ ከእርሱ ጋር ኪዳን ገባ፣ ዳዊት ንጉሥ እንደሚሆንና መንግሥቱ የእርሱ መንግሥት እንደሚሆንም ተነበየ—1 ሳሙ. 18፡1-4፤ 19፡1-7፤ 20፡8፣14-17፣41-42፤ 23፡16-18፡-

ሀ. የሳኦል ውጥን መንግሥቱን ለዮናታን ለማቆየት ነበር፤ ሆኖም ግን ዮናታን መንግሥቱን ለመውሰድ ፈቃደኛ አልነበረም፣ ነገር ግን ዳዊት በዙፋኑ ላይ መሆን እንደሚገባው እውቅና ሰጠ።

ለ. ዮናታን ይህን በተመለከተ ለአባቱ መንገር ነበረበት፣ አባቱን ከዳዊት ጋር እንዲሆን መተው ነበረበት፤ በምሳሌ፣ ዮናታን ዳዊትን መከተሉ የእኛ ክርስቶስን መከተል እና ለእርሱ ፊተኛውን ስፍራ መስጠታችንን ያመለክት ነበር—ቆላ. 1፡18፤ ራእ. 2፡4።

ሐ. ዮናታን ለአባቱ በነበረው ተፈጥሯዊ ፍቅር በእግዚአብሔር ፈቃድ መሠረት ዳዊትን ባለመከተሉ ውድቀት ምክንያት እግዚአብሔር በሰጠው ተስፋ መሠረት በመልካሚቱ ምድር የነበረውን ድርሻ ተገቢ እና አጥጋቢ ድሰታ አጣ፤ ምንም እንኳን ዳዊት እንደሚነግሥ ዮናታን ቢገነዘብም ከአባቱ ጋር ቆየ፣ ከዚህም የተነሳ እንደ አሳዛኝ ውጤት አባቱ የተቀበለውን ያንኑ እድል ፈንታ ተቀበለ፣ ከአባቱ ጋርም በውጊያ ሞተ—1 ሳሙ. 31፡2-6።

መ. ዮናታን በሳኦል እና በዳዊት መካከል ቆመ፤ በሁለት አገልግሎቶች መካከል የቆመ አንድ ሰው ነበር፤ ሁለተኛውን አገልግሎት መከተል ነበረበት፣ ነገር ግን ከመጀመሪያው አገልግሎት ጋር የነበረው ግንኙነት በጣም ጥልቅ ስለነበር ራሱን ማላቀቅ አልቻለም፡-

1. በእያንዳንዱ ዘመን ጌታ ሊፈጽማቸው የሚፈልጋቸው ልዩ ነገሮች አሉት፤ የራሱ ምለሳዎች እና ሊሠራቸው የሚፈልጋቸው የራሱ ሥራዎች አሉት፤ በአንድ ዘመን ውስጥ ያለው ልዩ ምለሳው እና የሚሠራው ሥራ የዚያ ዘመን አገልግሎት ነው—ተዛ. ዘፍ. 6፡13-14።
2. በዚያ ዘመን በነበረው አገልግሎት ዳዊት የዘመኑ አገልጋይ ነበር (ሐዋ. 13፡21-22፣36)፤ በብሉይ ኪዳን ኖኅ መርከብን የመገንባት የዘመኑ አገልግሎት ነበረው፣ ሙሴ የመገናኛ ድንኳን የመሥራት አገልግሎት ነበረው፣ ዳዊትና ሰለሞን መቅደስ የመገንባት የዚያ ዘመን አገልግሎት ነበራቸው።
3. ከዘመኑ አገልግሎት ጋር የዘመኑ አገልጋይ በአጥቢያ ካሉ አገልጋዮች ይለያል፤ ሉተር የዘመኑ አገልጋይ ነበር፣ ዳርቢም እንዲሁ የዘመኑ አገልጋይ ነበር፤ የዚህ ዘመን አገልግሎት በደረሰበት ለመድረስ የእኛ ራእዩን የማየት ፍላጎት አለ፤ ሚልኮ ዳዊትን አግብታ ነበር፣ ሆኖም ግን ምንም አላየችም ነበር፤ ያየችው የዳዊትን ውጫዊ ሁኔታ ብቻ ነበር፣ ልትታገሰውም አልቻለችም፤ ከዚህም የተነሳ ወደ ኋላ ቀርታለች—2 ሳሙ. 6፡16፣ 20-23።
4. በአዲስ ኪዳን የጌታ ኢየሱስ አገልግሎት ቤተ ክርስቲያንን እንደ ክርስቶስ አካል መገንባት ነው (ማቴ. 16፡18)፤ ጌታ በዕርገቱ ያፈራቸው ብዙዎቹ ስጦታ ያላቸው ሰዎች አንድ አገልግሎት ብቻ አላቸው፣ ይህም፣ ለቤተ ክርስቲያን፣ ለክርስቶስ አካል መገንባት ክርስቶስን ለሌሎች ማገልገል ነው፤ ይህ ግንባታ ስጦታ ባላቸው ሰዎች በቀጥታ አይከናወንም፣ ነገር ግን በእነዚህ ስጦታ ባላቸው ሰዎች ፍጹማን በተደረጉት ቅዱሳን ይከናወናል (ኤፌ. 4፡11-12፣16)።
5. በእግዚአብሔር የግንባታ አገልግሎት በእያንዳንዱ ዘመን በዚያ አገልግሎት ቅድሚያውን የሚወስዱ አሉ፤ ሰዎች እስከሆንን ድረስ ክርስቲያኖች መሆን እንዳለብን እናይ ዘንድ ጌታ ዓይኖቻችንን ይክፈትልን፤ ክርስቲያኖች እስከሆንን ድረስ በዚህ ዘመን ባለው የጌታ አገልግሎት ውስጥ መግባት አለብን።

6. አንድ ሰው የዘመኑን አገልግሎት ማየት መቻሉ እና ከዚህ አገልግሎት ጋር መገናኘት መቻሉ የእግዚአብሔር ምሕረት ነው፣ ሆኖም ግን የአንድ ሰው ያለፉትን አገልግሎቶች የመተው እና ወደ የጊዜው የእግዚአብሔር አገልግሎት ውስጥ የመግባት ድፍረት ሙሉ በሙሉ የተለየ ነገር ነው—ተዛ. 1ሳሙ. 14፥1-46፤ 2ሳሙ. 6፥16፣ 20-23።
7. የዘመኑ አገልግሎት የአሁኑን እውነት ለእግዚአብሔር ሕዝብ ያገለግላል፤ በ 2ኛ ጴጥ. 1፥12 *በእናንተ ዘንድ ያለ እውነት* የሚለው "የዳበረው የአሁኑ እውነት" ተብሎ ሊተረጎም ይችላል፤ እያንዳንዱ የጌታ ሠራተኛ የአሁኑ እውነት ምን እንደሆነ እግዚአብሔርን መጠየቅ አለበት—ማቴ. 16፥18፤ ኤፌ. 4፥15-16፤ ራእ. 2፥7፣ 11፣ 17፣ 26-29፤ 3፥5፣ 12፣ 21፤ መዝ. 48፥2፤ ራእ. 19፥7-9፤ 21፥2።

## IV. ሳኦል በእግዚአብሔር ተመርጦ ነበር፣ እና የእስራኤል ንጉሥ ለመሆን በሳሙኤል ተቀብቶ ነበር—1 ሳሙ. 9፥1-2፣ 17፤ 10፥1፣ 24፡-

ሀ. ሳኦል የእግዚአብሔርን ቃል ቢያንስ ለሁለት ጊዜ አልታዘዘም፣ ከዚህም የተነሳ ንግሥናውን እና መንግሥቱን አጣ (13፥13-14፤ 15፥19፣ 23፤ 28፥17-19)፤ በ 1ኛ ሳሙኤል 15 ሳኦል እግዚአብሔርን ባለመታዘዙ በእርሱ ላይ ዓመፀ።

ለ. በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ሳሙኤል ሳኦልን "ዓመፀኝነት እንደ ምዋርተኛ ኃጢአት፥ እልከኝነትም ጣዖትንና ተራፊምን እንደ ማምለክ ነው" (ቁ.23) ብሎ ተናገረው፤ ምዋርተኝነትን መለማመድ ከክፉ መናፍስት ጋር ግንኙነት ማድረግ ነው፤ ሳኦል በእግዚአብሔር ላይ በማመፁ ያደረገው ነገር ልክ እንደዚህ የምዋርተኝነት ኃጢአት ነው፤ ለእግዚአብሔር አልተገዛም ነበር፣ እንዲያውም የእግዚአብሔር ጠላት ሆነ፤ ከዚህም የተነሣ ንግሥናውን አጣ።

ሐ. የሳኦል አሳዛኝ መጨረሻ ከእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ጋር ተገቢ በሆነ መንገድ ባለመገናኘቱ ምክንያት ነበር፤ እግዚአብሔር በተመረጡት ሕዝቡ መካከል መንግሥቱን ለመገንባት በመፈለግ፣ ሳኦልን ወደ ኢኮኖሚው ውስጥ አምጥቶት ነበር፣ ነገር ግን በእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ከመሳተፍ እና ከኢኮኖሚው ጋር ከመተባበር ይልቅ ሳኦል ራስ ወዳድ ነበር፣ የራሱን ንጉሠ-ነገሥትም ለመገንባት የእግዚአብሔርን መንግሥት አለአግባብ ያዘ፤ ልጁ እንዴት ከእርሱ ቀጥሎ እንደሚነግሥ ማሰብን ጨምሮ በንግሥና ሃሳቦች ተሞላ—20፥31።

መ. በዚህ ሳኦል ራስ ወዳድ እና ሙሉ በሙሉ ተሳስቶ ነበር፤ በስተመጨረሻ እግዚአብሔር ሳኦልን ተወው፣ መንግሥቱንም ከእርሱ በመቅደድ ሳኦልን አስወገደው (15፥28)፤ ሳኦል በእግዚአብሔር ስለተተወ ችግር ሲመጣ የእርዳታ አቅርቦት እስከሚያጣ ድረስ እንደ ጉድፈቻ ብቻውን ቀረ።

ሠ. ከሳኦል ራስ ወዳድነት የተነሳ የእስራኤል ልጆች ተሸነፉ፣ እናም ከፍልስጤማውያን ጋር በነበራቸው ውጊያ ተገደሉ፣ ሳኦልና ልጆቹም ተገደሉ፤ የሳኦል በዳዊት ላይ ከመቅናቱ ጋር መንግሥቱን ለራሱና ለልጁ የማድረግ ምኞቱ፣ በእግዚአብሔር ተስፋ ለተሰጠው መልካሚቱ ምድር የነበረውን ድስታ ወሰደበት፣ ደመደመውም—20፥30-34።

ረ. የሳኦል፣ የሦስቱ ልጆች እና የጋሻ ጃግሬው የሁሉም ሞት በእግዚአብሔር ላይ ላመፁበት፣ እርሱን አለአግባብ ለተጠቀሙበት እና ጠላቶቹ ለሆኑት የእግዚአብሔር ፍትሃዊ ፍርድ ነበር (1 ዜና. 10፥13-14)፤ ከሳኦል አሳዛኝ መጨረሻ ልንማረው የሚገባ ትምሕርት ሥጋችንን የመስቀል እና ራስ ወዳድነታችንን፣ የግል ጥቅምን እና ለራስ የሆነን ነገር መፈለግን መካድ ነው (ገላ. 5፥24፤ ማቴ. 16፥24፤ ፊልጵ. 2፥3)።

ሰ. የሳኦልን አሰቃቂ መጨረሻ የተመለከተው ዘገባ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለሚያገለግሉ ሁሉ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ የተነጠለ ሥራ እንዳይሠሩ ወይም በመንግሥቱ ውስጥ ያለውን ማንኛውም ነገር አለአግባብ እንዳይጠቀሙ ጠንካራ ማስጠንቀቂያ ነው፤ ለራሳችን "ንጉሠ-ነገሥት" ለመገንባት በመሞከር እንደ ሳኦል መሆን የለብንም፤ ይልቁንም ሁላችንም የእግዚአብሔርን መንግሥት፣ የክርስቶስን አካል የመገንባት ልዩ እና ብቸኛ የሆነውን አንድ ሥራ መሥራት አለብን—1 ሳሙ. 31፥1-13።

## V. ዳዊት የእስራኤል ንጉሥ ይሆን ዘንድ በሳሙኤል በኩል በእግዚአብሔር ተመረጠ፣ ተቀባም—16፥1፤12-13፡-

ሀ. ዳዊት ጎልያድን በሰይፍ ከገደለው በኋላ ከሳኦል እንደሚበልጥ በእስራኤል ሴቶች ተወደሰ (18፥7)፣ ነገር ግን ዳዊትን በተመለከተ እንደ ታበየ ወይም ንግሥናን ለመውሰድ ምኞት እንደነበረው ምንም የሚያመለክት ነገር የለም፤ በሳኦል ስደት ሥር ዳዊት ሲፈተን የእግዚአብሔርን መንግሥት በምድር ላይ በመመሥረት የእግዚአብሔርን ኢኮኖሚ ለማከናወን ትክክለኛው ሰው ለመሆኑ ተቀባይነትን አገኘ።

ለ. ዳዊት በሳኦል ስደት ሥር ሳለ ሳኦልን ለማጥፋት ሁለት እድሎች ነበሩት፣ ነገር ግን ሳኦል በእግዚአብሔር በመቀባቱ ዳዊት ለእግዚአብሔር ከነበረው ፍርሃት የተነሳ ይህን አላደረገም፤ ዳዊት በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ መልካም ሥርዓት መጠበቁን ይህ ያመለክታል—ምዕ. 24 እና 26፤ ተዛ. ሮሜ. 12፥3።

ሐ. ዳዊት እንደ እግዚአብሔር ልብ የሆነ ሰው በመሆኑ መሠረት ለእግዚአብሔር ዓላማ መሟላት፣ ያለጥርጥር ራሱን አለመበቀል ነገር ግን ራሱን መካድ ተማረ—1 ሳሙ. 13፥14።

መ. በእግዚአብሔር ለተመረጠው ሕዝቡ ተስፋ የተገባችውን እና የተሰጠችውን መልካሚቱን ምድር በመደሰት ዳዊት እውነተኛ የእስራኤል ልጅ ሞዴል ነው፤ በእግዚአብሔር ታምነ፣ በእግዚአብሔር ሉዓላዊነትም መሠረት እና በፈተናዎቹም ሁሉ በእግዚአብሔር ምሪት እና ትዕዛዝ መሠረት ከእግዚአብሔር ጋር ተራመደ፤ ዳዊት የእግዚአብሔርን ርስት በመካፈል እና እርሱን በማገልገል በመልካሚቱ ምድር መቆየትን ተጠባበቀ—17፥36-37፤ 23፥14-16፤ 30፥6-10፤ 26፥19።

ሠ. የዳዊት አውነተኛ በእግዚአብሔር ላይ መታመን እና በታማኝነት የተሞላው ከእግዚአብሔር ጋር የነበረው ምልልስ፣ ሙሉ በሙሉ ከፍተኛ በሆነ ደረጃ፣ በእግዚአብሔር ልብ መሠረት በምድር ላይ የእግዚአብሔር መንግሥት እስከሆነው ንግሥና ድረስ መልካሚቱን ምድር ለመደሰት አበቃው፤ ዳዊት ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ነበር፤ የእርሱ የነበረው የእግዚአብሔር ነበር፣ የእግዚአብሔር የነበረውም የእርሱ ነበር፤ እርሱ እና እግዚአብሔር አንድ መንግሥት ብቻ ነበራቸው፤ እንዲህ ያለው ሰው ክርስቶስን የምታመለክተውን መልካሚቱን ምድር ፈጽሞ ተደሰተ።

ረ. ከሳኦል ሞት በኋላ "በሳኦል ቤትና በዳዊት ቤት መካከል ብዙ ዘመን ጦርነት ሆነ፤ የዳዊት ቤት እየበረታ፥ የሳኦል ቤት ግን እየደከመ የሚሄድ ሆነ" (2 ሳሙ. 3፥1)፤ ለእግዚአብሔር ሕዝብ ለእስራኤል ሲባል ከፍ ይደረግ ዘንድ ዳዊት ከመንግሥቱ ጋር እንደ ንጉሥ በእግዚአብሔር ተመሠረተ፤ በተጨማሪም "ዳዊትም እየበረታ ሄደ፤ የሠራዊት አምላክ እግዚአብሔርም ከእርሱ ጋር ነበረ" (ቁ.10)፤ ዳዊት የእግዚአብሔር መገኘት እንደነበረው ይህ ያመለክታል።

ሰ. በምንም ጉዳይ ጌታ ከእኛ ጋር እንደሆነ የውስጥ ስሜት ከሌለን መጠንቀቅ እና መንገዳችንን እንደገና ማሰብ አለብን (1 ሳሙ. 16፥14)፤ በጌታ ምለሳ ውስጥ ማንኛውንም ነገር ስናደርግ ለጌታ መገኘት ስሜት መጠንቀቅ አለብን፤ ሁላችን ለሁለት ነገሮች መጠንቀቅን መማር ያስፈልገናል፡- የእግዚአብሔር የውስጥ መገኘት እና በከባቢ ሁኔታችን ያለ ውጫዊ ማረጋገጫ (ተዛ. 2 ሳሙ. 5፥11-12)።

ሸ. በተጨማሪም፣ በአሉታዊ ጎኑ እንዲሁም በአዎንታዊ ጎኑ ከዳዊት መማር አለብን፤ የሥጋ ምኞት ሊያጠፋን የሚችል አውዳሚ ንጥረ-ነገር ነው፤ እንደ ዳዊት ያለ የእግዚአብሔር ሰው ሊታለል ከቻለ እኛስ እንዴት ልናመልጥ እንችላለን?—11፥1-27፤ ተዛ. 2 ጢሞ. 2፥22፤ 1 ቆሮ. 6፥13፣18፡-

1. በመንፈሳዊ ግስጋሴያችን ምንም አይነት ደረጃ ላይ ብንደርስም፣ ማናችንም እንደዚህ አይነት ኃጢአት ልንፈጽም እንችላለን፤ ይህን ጉዳይ በጌታ መገኘት ውስጥ በትኩረት መመልከት አለብን፤ የሥጋ ምኞት ከባድ ነገር እንደሆነ ይህ ታሪክ ያስጠነቅቀናል፤ ዳዊት የተፈተነው በአንድ እይታ ብቻ ነው፣ ከዚያም ራሱን መገደብ አልቻለም።
2. ቅዱሳን በሙሉ፣ በተለይ ደግሞ ወጣቶች፣ ልባቸውን መፈተሽ እና በሥጋ ምኞት መንገድ ፈጽሞ ላለመሄድ የልብ ጠንካራ ውሳኔ መወሰን አለባቸው (መሳ. 5፥15-16)፤ "ጌታ ኢየሱስ፣ እወድሃለሁ፣ ታስፈልገኛለህ፣ እቀበልሃለሁ" ማለት ያስፈልገናል፤ ይህን ካልን አዳኛችን እና አንቀሳቃሽና ኃይለኛ ድነታችን ይሆናል፤ የደረስንበትን ክብር እንጠብቅ ዘንድ እንደ እስትንፈሳዋዊው ክርስቶስ እርሱ ያድነናል፣ ይጠብቀናል፣ ከዚህ ዘመን ብክለትም ይጋርደናል።

© 2021 Living Stream Ministry